# የብሉይ ኪዳን በዓላት

## ሰባቱ የብሉይ ኪዳን በዓላት እና ትርጉማቸው

በጃኪ አንደርሰን ተጽፎ
በጳውሎስ ኮይቴ የተተረጎመ

| በዓል | መታሰቢያ | ጠቀሜታው | ትንቢታዊ ትርጉም |
|---|---|---|---|
| 1. ፋሲካ አንድ ቀን | እግ/ር የእስራኤላዊያን በኩር ልጆች ከሞት ያዳነበት | -እግ/ር ሕዝቡን ያዳነበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | ኢየሱስ ስለሐጢአ-ታችን በግ ሆኖ ተሰዋልን፡፡ |
| 2. የቂጣ በዓል ሰባት ቀን | እስራኤላዊያን ከግብፅ ባርነት ነጻ የወጡበት | -ሕዝቡ ከአሮጌው ሕይወት ወደ አዲስ ሕይወት የተሻገሩበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | ኢየሱስ ከሐጢአታ-ችን ነፃ አወጣን፡፡ |
| 3. የበኩራት በዓል አንድ ቀን | የመጀመሪያውን የገብስ እህል የሰበሰቡበት | -እግ/ር ሕዝቡን በእህል የባረከበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | የኢየሱስ ትንሳኤ አዲስ ሕይወት |
| 4. ጴንጠቆስጤ አንድ ቀን | የገብስ ሰብል ያለቀበትና የስንዴ እህል የደረሰበት | -ሕዝቡ በእግ/ር የተደሰቱበትና እግ/ርን ያመሰገኑበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | የመንፈስ ቅዱስ መምጣት የቤ/ክርስቲያን መጀመሪያ |
| 5. የመለከት ድምጽ አንድ ቀን | አዲስ ዓመት መጀመሪያ | -ምስጋናና ደስታን ያስታውሳል፡፡ | የኢየሱስ ዳግም መምጣት |
| 6. የስርየት በዓል አንድ ቀን | እግዚአብሔር የሕዝቡንሐጢአት ይቅር ያለበት | - ሕዝቡ ከእግ/ር ጋር ግንኙነት ያደረጉበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | አማኞች የኢየሱስን ሞት ተቀበሉ |
| 7. የመገናኛው ድንኳን ሰባት ቀን | እግ/ር ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራበት | -እስራኤዊያን ከእግ/ር ጋር ግንኙነታቸውን ያደሱበትን ጊዜ ያስታውሳል፡፡ | በአዲስቷ ኢየሩሳ-ሌም ከእግዚአብ-ሔር ጋር መኖር |

# የብሉይ ኪዳን ግብዣ በዓላት

## አንደኛ፡- የፋሲካ በዓል

**መግቢያ፡-** እሥራኤላዊያን በግብፅ ምድር ይኖሩ ነበር፡፡ ፈርኦን ባሪያ አድርጎ ገዛቸው፡፡ ከዚያም ያህዌ (እግዚአብሔር) ሙሴን ልኮ ይህን ሕዝብ ከባሪነት ምድር አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲመራቸው አደረገ፡፡ ነገር ግን ፈርኦን ሕዝቡን አልለቅም አለ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ዘጠኝ መቅሰፍቶችን ላከባቸው፡፡ በዚህ ሁሉ ፈርኦን ሕዝቡን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር አሥረኛውን መቅሰፍት ልኮ የግብፅን በኩር ሁሉ እንዲሞቱ አደረገ፡፡
ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

በዘፀ፡11 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

የበኩር ልጆቻቸው እንዳይሞቱ እግዚአብሔር ለእሥራኤላዊያን መመሪያ ሰጠ፡፡ ዘፀ፡12፡1-14 ላይ ስለ ፋሲካ አንብብ፡፡ በመቀጠል የክፍሉን ጠቅላላ መልእክት የያዙትን ጥያቄዎች መልስ፡፡

**ምልከታ (የክፍሉ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)፡- ፋሲካ ምንድነው?**

1. ለፋሲካ  በዓል የተመረጠው በግ ምን ዓይነት እንደሆነ ግለጽ፡፡ (ቁ.5)
2. ሕዝቡ ይህን በግ ምን ማድረግ ነበረባቸው? (ቁ.6 እና 7)
3. ምግብ እንዴት መበላት እንዳለበት እግዚአብሔር የሰጠው መመሪያ ምን ነበር? (ቁ.8)
4. በፋሲካው ምሽት እግዚአብሔር ምን አደረገ? (ቁ.12)
5. ደሙ በጉበኑ ላይ ቢቀባ ምን ይሆን ነበር? ባይቀባስ ምን ይሆን ነበር? (ዘፀ፡12፡23 እና ቁ.29-27 አንብብ፡፡)
6. ዘለዋ፡23፡5 አንብብ፡፡ ይህ ፋሲካ በዓል ዛሬ በክርስቲያኖች ዘንድ በየዓመቱ ለመታሰቢያነት ይከበራል፡፡ ይህ ፋሲካ መቼ ጀመረ? የጀመረበት ቀን ምን ነበር? የጀመረበት ሰዓቱስ?

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**፡- የዚህ በዓል ጥቅሙ ምን ነበር

7. ይህን ታሪካዊ ክስተት እሥራኤላዊያን ለምን ማሰብ አስፈለጋቸው? (ቁ.14 እና 26-27)
8. በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በ_______________መስዋእት ፋንታ የ______________መስዋእት ይቀበል ነበር፡፡
9. ደምን በጉበኑ ላይ ማድረግ ያስፈለገው ለምን ነበር? ይህ ደምን በጉበኑ ላይ ማድረግ በእግዚአብሔርና በእሥራኤላዊያን መካከል ምን እንዳለ ያሳያል?
10. የብሉይ ኪዳን በግ የክርስቶስ ጥላ ነበር፡፡ አሁን ወደ ዘፀ፡12 ተመለስና ይህ የመስዋእት በግና ኢየሱስ እንዴት እንደሚመሳሰሉ ጻፍ፡፡
11. ዘፀ፡12 እና ዮሐ፡19፡32-36 አንብብ፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች ምን ትማራለህ?
12. ከዚህ በታች ያሉትን ክፍሎች አንብብና ስለ አዲስ ኪዳን በግ የምትማረውን ተወያይ፡፡

ሀ. 1ቆሮ፡5፡7
ለ. ዮሐ፡1፡29
ሐ. ራዕ፡5፡12

13.ስለ ክርስቶስ ደም ከሚከተሉት ክፍሎች የምንማረው ምንድነው?
ሀ. ሮሜ፡5፡8-10
ለ. 1ጴጥ፡1፡18-19

14.ደምን በጉበኑ ላይ ማድረግ የእምነት ምልክት ነው፡፡ የሚከተሉትን ክፍሎች አንብብ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ በግ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ደሙ በጉበኑ ላይ ይደረግ ነበር ይህን ዛሬ እንዴት ከሕይወታችን ጋር ማዛመድ እንችላለን?

ሀ.ዮሐ፡3፡16-18
ለ.ዮሐ፡20፡31
ሐ.1ዮሐ፡5፡13

<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u> **ይህ የፋሲካ በዓል ለእኔ ምን ማለት ነው?**

በጉበኑ ላይ ያለውን ደም እግዚአብሔር አይቶ የሞት መልዓክ ያንን ቤት ሳይነካው እንዲያልፍ አደረገ፡፡ እግዚአብሔር ዛሬ አንተን ሲመለከት በአንተ ውስጥ ምን ያያል?

ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ከደቀመዛሙርቱ ጋር ካከበረ በኋላ የፋሲካ በግ ሆኖ ለእኛ በመስቀል ላይ ተሰዋልን፡፡ በኢየሱስ የተመሠረተ አዲስ ግብዣ አለን፡፡ ኢየሱስ በሉቃ፡22 ላይ በጀመረው አዲስ ኪዳን ግብዣ ላይ መሳተፍ ለምን ያስፈልጋል?

የፋሲካው በዓል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያመጣው የደህንነት ታሪክ መጀመሪያ ነው፡፡ ደህንነት ማለት የሐጢአትን ዋጋ ከፍሎ ሰዎችን ከግዞት ነፃ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ስለ ደህንነትህ እግዚአብሔርን እንድታመሰግን ከዛሬው ታሪክ የተማርከው ምንድነው?

## <u>ሁለተኛ፡- የቂጣ በዓል</u>

**ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፡-** ባለፈው ሳምንት ስለ ፋሲካ በዓል ተምረን ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የነበረውን ሕዝብና የሚመጣውን ትውልድ ስለ ራሱ ለማስተማር እግዚአብሔር እነዚህን በዓላት አደረገ፡፡ ዛሬ ከፋሲካ በዓል ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ስለ ጀመረው ሌላ በዓል እንማራለን፡፡

**<u>ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)፡-</u> የቂጣ በዓል ምንድነው?**

ዘፀ፡12፡14-20 እና ዘፀ፡13፡3-10 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡

1. ይህ በዓል መቼ ተደረገ? በስንት ቀን አለቀ?

2. በበዓሉ መጀመሪያ ቀን ምን አደረጉ?
3. በበዓሉ መጨረሻ ቀን ምን አደረጉ? ዘፀ፡13፡6
4. በእነዚህ ሰባት ቀናት ምን እንዳደረጉ ግለጽ::
5. ስለ እርሾ የሚያወሩ ክፍሎችን ተመልከት። ስለ እርሾ ምን ትማራለህ?
6. ከቁ.14 ምን ትማራለህ?
7. በቁ.17 እግዚአብሔር ለበዓሉ የሚሰጠው ምክንያት ምንድነው? በዘፀ፡13፡3 ላይ ሙሴም የሚሰጠው ምክንያት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው።
8. ለልጆቻቸው ምን መናገር ነበረባቸው? 13፡8

<u>**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**</u> ይህ በዓል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን ያስተምረናል?

1. ፋሲካ የሚከበረው ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ ስለሆነ ነው። ይህ በዓል የተከበረው ከባሪነት ቀንበር ነፃ ስለወጡ ነው። ሕዝቡ ነፃ የወጣው ምን ለማድረግ ነበር?
2. ቀጥሎ ያሉት ክፍሎች ስለ እርሾና ሐጢአት ያወራሉ። እርሾ እንዴት በሐጢአት ይመሰላል?

   ሀ. 1ቆሮ፡5፡8
   ለ. 1ቆሮ፡5፡7
   ሐ. 1ቆሮ፡5፡8
3. በ1ቆሮ፡5፡7-8 ላይ በራሳቸው የሚቃረኑ ሀሳቦች የትኞቹ ናቸው? ከዚህ በታች ያለውን ባዶ ቦታ ሙላና ምን እንደተማርክ ተወያይ።

| | |
|---|---|
| ሀ. አሮጌ | አዲስ |
| ለ. ለፈርኦን ታዘዙ | ለ____________ታዘዙ |
| ሐ. ያለፈው ሕይወት | የ______________ሕይወት |
| መ. ክፋትና____________ | ቅንነትና____________ |

ፋሲካ በአንድ ቀን ይከበራል። የቂጣ በዓል ግን ሰባት ቀን ይቆያል። የመስቀሉ ሥራ በአንድ ቀን ተፈጸመ። እግዚአብሔርን በነጻነት ለማገልገል ያገኘነው አዲስ ሕይወት በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ቀጣይ ነው።

4. በሉቃ፡22፡15-20 ላይ ኢየሱስ በፋሲካው በዓል ጊዜ እርሾ ያልገባበትን ቂጣ አንስቶ ስለ ራሱ ምን አለ? 1ዮሐ፡3፡5ንም አንብብ።

<u>**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**</u> ከዚህ ታሪክ ለሕይወቴ ምን እማራለሁ?

1. ከሐጢአት በመራቅ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነታችንን እንድናጠብቅ ከዚህ በታች ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምን ያስተምሩናል?

   ሀ. 2ቆሮ፡7፡1
   ለ. ኤፌ፡4፡22-32
2. እርሾው መወገድ ያለበት ከየትኛው ቦታ እንደሆነ ተመልከት።
   ይህ ለሕይወትህ ምን ማለት ነው?
   ሀ. ዘፀ፡12፡15 ከቤታችሁ አስወግዱ
   ለ. ዘፀ፡12፡15 ከሕይወታችሁ አስወግዱ

ሐ. ዘፀ፡13፡6-7 ከመካከላችሁ አስወግዱ

2. ፀልይና በሕይወትህ፣በቤትህና ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ባለህ ግንኙነት እርሾ ያለበትን ቦታ በጥንቃቄ እይና አስወግድ፡፡ ልጆችህ ሲጠይቁ ምን ታደርጋለህ? ዘፀ፡13፡8 ላይ ያለውን ታስታውሳለህ፡፡
3. ሕይወትህን ነፃ ለማድረግ ዳዊት የፀለየውን ፀሎት ተጠቀም፡፡ መዝ፡139፡23-24
   አቤቱ፣ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፣
   ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ፣
   በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፣
   የዘላለምንም መንገድ ምራኝ::

## ሦስተኛ፡- በመጀመሪያው ፍሬ የሚያከብሩበት በዓል

***መግቢያ፡-*** እግዚአብሔር ለእሥራኤላዊያን ሦስተኛና አስፈላጊ በዓል አደረገ፡፡ እሥራኤላዊያን ከግብፅ ባሪነት ነፃ ከወጡ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት አዲስ ግንኙነት አደረጉ፡፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ ማርና ወተት በሚታፈልቀው ምድር እንደሚኖሩ እግዚአብሔር ተናገረ፡፡ መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዳይዘነጉ እግዚአብሔር ፈለገ፡፡ ከዚህ በዓል እግዚአብሔር ብዙ ነገር እንዲያስተምርህ ፀልይ፡፡

**ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)**

**ይህ በመጀመሪያው ፍሬ የሚያከብሩት በዓል ምንድነው?**

1. ዘሌዋ፡23፡9-14 አንብብ፡፡
2. ይህ በዓል የት መከበር ነበረበት? ቁ.9 እና 10
3. ይህ በዓል መቼ መከበር ነበረበት? ቁ.11-14
4. ይህንን በዓል ማክበር ያለበት ማነው?
5. በበዓሉ ጊዜ ማድረግ የነበረባቸውን ነገር ግለጽ፡፡
6. ከዚህ ሌላ የሚታይ ነገር አለ? ካለ በላይ ከተጠቀሱት ላይ ጨምር፡፡
7. ዘዳ፡26፡1-11 አንብብ፡፡ ከተሰበሰበው መከር በኩራትን ለእግዚአብሔር መስጠት ያስፈለገው ለምንድነው?

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**

1. የሚከተሉትን ክፍሎች አንብብ፡፡ ይህን በዓል ትንቢት ክርስቶስ እንዴት ፈጸመው?
   ሀ. 1ቆሮ፡15፡20-23
   ለ. ሮሜ፡8፡29
2. በማር፡16፡1-8 ላይ የክርስቶስ ትንሣኤ ታሪክ አንብብ፡፡
   ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው በሣምንቱ በየትኛው ቀን ነበር? የመከሩ የመጀመሪያው ፍሬ (በኩራት) በዓል የተከበረው በሣምንቱ በየትኛው ቀን ነበር? ከዚህ ምን ትማራለህ?

3. ኢየሱስ የትንሣኤ በኵር ነበር፡፡ ስለቀሪዎቹ የመከር አጨዳዎች በዓላት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምረናል?
   1ቆሮ፡15፡43-57 አንብብ፡፡

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u> እኔ ምን እንዳደርግ ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው?**

1. በኩራትን ለእግዚአብሔር ስለመስጠት የሚከተሉት ክፍሎች ምን ያስተምሩናል?
   ሀ. ምሳ፡3፡9
   ለ. 1ቆሮ፡16፡2
   ሐ. 2ቆሮ፡9፡6-11
   መ. ዕብራ፡13፡15
2. በእግዚአብሔር መከር የበኩር ስጦታ ስለሆነው ኢየሱስ ዛሬ እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡
3. ከዚህ ትምህርት ዛሬ እግዚአብሔር ሊያስተምርህ የሚፈልገው ምንድነው? በሚመጣው ሣምንት ምን ታደርጋለህ?

## <u>አራተኛ፡-የሳምንታት ወይም የጴንጠቆስጤ (በዓለ ሃምሳ ቀን) በዓል</u>

***<u>መግቢያ</u>*፡- አራተኛው በዓል የሳምንታት ወይም የጴንጠቆስጤ በዓል ይባላል፡፡ ይህ ጴንጠቆስጤ የተባለው በዓል ስም ያገኘው ሕዝቡ በመጀመሪያው ፍሬ እግዚአብሔርን የሚያከብሩበት በዓል ካለፈ በኋላ ሰባት ሳምንታትን ስለቆጠሩ ነው፡፡

**<u>ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)</u>**
**ይህ የሳምንታት በዓል የሚባለው ምንድነው?**

ዘሌዋ፡23፡15-22 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ፡፡

1. ይህ በዓል የጀመረው መቼ ነበር?
2. በዚህ በዓል ጊዜ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ተወያይ፡፡
3. በዚህ በዓል እሥራኤላዊያን ምንን እያሰቡ ማክበር ነበረባቸው? ወይም ይህንን በዓል በየዓመቱ እንዲያከብሩ እግዚአብሔር ቀድሞ ያደረገላቸው ነገር ምን ነበር?
4. የዚህ በዓል ሌላ ስሙ የሳምንታት በዓል ይባላል፡፡ ጴንጠ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ሃምሳ (50) ማለት ነው፡፡ ጴንጠቆስጤ የሚለው ቃል ከዚህ ነው የተገኘው፡፡
5. በዚህ ክፍል አምስት የተለያዩ መስዋእቶች ተጠቅሰዋል፡፡ ለመስዋእትነት የቀረቡ ነገሮች ምንድናቸው?
   ሀ. የመወዝወዝ እንጀራ መስዋእት
   ለ. የሚቃጠል መስዋእት
   ሐ. ለሐጢአት የሚቀርብ መስዋእት
   መ. የተቀደሰ ጉባኤ መስዋእት
   ሠ. የመጠጥ መስዋእት

6. የመወዝወዝ እንጀራ መስዋእት ከአዲሱ የበጋ ስንዴ የተዘጋጀ ነበር፡፡ ስንት እጅ ዱቄት ነበር ለዚህ ያስፈለገው?
7. ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ከክፍሉ የሚታይህ ሀሳብ አለ?

## <u>የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች</u>

## የዚህ በዓል ትንቢታዊ ጠቀሜታ ምን ነበር?

1. የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ ከ50 ቀን በኋላ ምን ሆነ?
   ሀ. ሐዋ፡1፡1-8
   ለ. ዮሐ፡14፡16-17
   ሐ. ሐዋ፡2፡1-4
2. ጴንጠቆስጤ የቤክርስቲያን መሠረት መጀመሪያ ነው፡፡ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማንበብ ቤተክርስቲያን የጀመረችበትን ጊዜ ተመልከት፡፡ ከዚህ ምን ትማራለህ?
   ሀ. ዮሐ፡7፡39
   ለ. ሐዋ፡1፡4-5
   ሐ. 1ቆሮ፡12፡12-13 ይህ ሁለት የመወዝወዝ እንጀራ መስዋእት በዚህ ክፍል የሚወክለው ምንድነው? (ለዚህ ፍንጩ፡ ሁለት ዓይነት ሰዎች የሚለው ነው)
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን ምን ይላል?
   ሀ. ኤፌ፡3፡5-6
   ለ. ያዕ፡ 1፡18
   ሐ. ኤፌ፡11-16

## <u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u> ከዚህ በዓል የምማረው ምንድነው?

1. በአይሁድ የሳምንታት በዓል የሚባለው ሕዝቡ መከር በሚሰበስቡበት ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምስጋና ጊዜ ነበር፡፡ ይህ በዓል ለቤተክርስቲያን መወለድ ትንቢት ነበር፡፡ ብዙ አዲስ ሰዎች በጴንጠቆስጤ ቀን ጌታን ተቀበሉ፡፡ አይሁዶች በዚያን ጊዜ መከር አጭደው እንደሰበሰቡ ይህም የጴንጠቆስጠ በዓል የነፍሳት መከር የሚሰበስብበት ቀን ነበር፡፡ እነዚህ ጌታን የተቀበሉ ሰዎች ከተለያየ ወገን የመጡ አይዶች ነበሩ፡፡ በኋላም አሕዛብም ጌታን ስለተቀበሉ የዚሁ መከር አካል ነበሩ፡፡ ይህ አንተን እንዴት ያበረታታሃል? ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
2. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን እንደመከር ሰበሰበ፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላሉ አባላት ያለን ሃላፊነት ምንድነው?
3. የመንፈስ ቅዱስ መምጣት እንዴት አንድ አካል እንድንሆን ሊረዳን ይችላል?
4. ከሳምንታት ወይም ከጴንጠቆስጠ በዓል ዛሬ ምን ተምረሃል?

## አምስተኛ፡- የመለከት ድምጽ በዓል

***መግቢያ፡-*** ይህ የሚገርም በዓል ነው ምክንያቱም መለከት ወይም ቀንደ መለከት የሚነፋው ለብዙ ምክንያቶች ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመሰብሰብ ይጠቀማል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለጦርነት ይጠቀማል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ንጉሥን ለመሾም ይጠቀማል፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምህረት ሲያደርግ የሚነፋ መሣሪያ ነበር፡፡

**ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)**

የመለከት ድምጽ በዓል ምንድነው?

ዘሌዋ፡23፡23-25 እና ዘኁል፡29፡1-6 ያለውን አንብብ፡፡

1. ይህ በዓል የጀመረው በየትኛው ወርና ቀን ነበር?
2. በቀኑ ሕዝቡ ምን እንዳደረጉ ግለጽ፡፡
3. ዘኁል፡10፡1-10 አንብብ፡፡ መለከቱ ከተነፋበት ዓላማዎች የተወሰኑቱ ምን ነበሩ?

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**

የዚህ በዓል ትንቢታዊ ጠቀሜታው ምን ነበር?

1. ኢዩ፡2፡1እና15 አንብብ፡፡ በዚህ ቦታ የመለከቱ ድምጽ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመሰብሰብ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ በዓል እንደሌሎች የተማርናቸው በዓላት የደስታ በዓል አልነበረም፡፡ ሕዝቡ ምን እንዲያደርጉ ነው ነብዩ ኢዩኤል የነገረው?
2. ከአሥር ቀን በኂላ በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ስለ ሐጢአታቸው እንደሚፈርድባቸው አዋጅ ተነገረ፡፡ ይህ አዋጅ የእግዚብሔር የማስጠንቀቂያ አዋጅ ነበር፡፡ ከሐጢአታቸው ንስሐ የሚገቡበትና ወደ ፍርድ እንዲቀርቡ የሚያደርግ አዋጅ ነበር፡፡ ከዚያም የፍርድ ቀን ካለፈ ከአሥር ቀን በኂላ ሕዝቡ ከሐጢአታቸው ንስሐ ስለገቡና ለእግዚአብሔር መስዋእት ስላቀረቡ እግዚአብሔር ምህረትን አወረደላቸው፡፡ በሚቀጥለው ትምህርታችን ስለ ፍርድ ቀንና እግዚአብሔር ለሐጢአት ስረየት ያደረገበትን እንማራለን፡፡
3. በራዕይ ላይ ያሉ ሰባቱ መለከቶች ስለ እግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ ማስጠንቀቂያና የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ያበስራሉ፡፡ ራዕ፡11፡15-19 አንብብ፡፡ ከዚህ ምን ትማራለህ?
4. የሚከተሉትን ትንቢታዊ ቃሎች አንብብና ስለ እሥራኤል የወደፊት መሰብሰብ ተወያይ፡፡
   ሀ. ኢሳ፡27፡12-13
   ለ. ሕዝ፡37፡21-23
   ሐ. ማቴ፡24፡27-31
5. ስለ ቤተክርስቲያን መሰብሰብ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምራል?
   ሀ. 1ተሰ፡4፡16
   ለ. 1ቆሮ፡15፡51-58

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**
እኔ ምን እንዳደርግ ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው?

1. እኛ ወደ ክርስቶስ ለመሰብሰብ ዝግጁ ሆነን መጠበቃችን ምን ያህል ጠቃሚ ነው?
   ሀ. 2ቆሮ፡5፡6-10
   ለ. ማቴ፡24፡42-44
2. ከመለከት ድምጽ በዓል ምን ተምረሃል? አንተ ምን እንድታደርግ እግዚአብሔር ይፈልጋል?

## ስድስተኛ፡- ለሐጢአት ስሪየት የሚደረግበት ቀን በዓል

***መግቢያ፡-*** ባለፈው ሳምንት ስለ መለከት ድምጽ በዓል ተምረን ነበር፡፡ ለሐጢአት ስሪየት የሚደረግበት ቀን ከመድረሱ አሥር ቀን በፊት ይህ የመለከት ድምጽ ተነፍቶ ነበር፡፡ በአይሁድ ሰዎች ዘንድ ‹ያም ክፑር› በመባል ስለ ሚታወቀው ስለዚህ በዓል ዛሬ እንማራለን፡፡ ‹ያም› ማለት ‹‹ቀን›› ሲሆን ‹ክፑር› ማለት ‹‹መሸፈን ወይም ስሪየት ማድረግ›› ማለት ነው፡፡ ይህ ቀን ራሳቸውን አዋርደው በእግዚአብሔር ፊት የሚጾሙበት ቀን ነበር፡፡

**ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)**
ለሐጢአት ስሪየት የሚደረግበት ቀን በዓል ምንድነው?

1. ዘሌዋ፡23፡26-32 አንብብ፡፡
   ሀ. ይህ በዓል መቼ ተደረገ?
   ለ. ይህ በዓል ለስንት ዓመት መከበር ነበረበት? ቁ፡31
   ሐ. በዚህ በዓል ጊዜ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ግለጽ፡፡
   መ. በዚህ ልዩ ቀን ራሱን ያላዋረደ ሰው ምን ይሆን ነበር?
2. ይህ ቀን በጣም አስፈላጊ ስለነበረ እያንዳንዱ ዝርዝር ሁኔታ በዘሌዋ፡16 ላይ ተገልጧል፡፡
   ዘሌዋ፡16፡6-22 እና ቁ.29-34 ያለውን አንብብ፡፡
   ሀ. ሊቀ ካህኑ ለሐጢአቱ ያቀረበው መስዋእት ምንድነው? ቁ.11
   ለ. ሊቀ ካህኑ ለመገናኛው ድንኳን ያቀረበው መስዋእት ምንድነው? ቁ.15-19
   ሐ. ሊቀ ካህኑ ለሕዝቡ ሐጢአት ያቀረበው መስዋእት ምንድነው? ቁ.20-22
   መ. ሊቀ ካህኑ በሕይወት ያለውን ፍየል ምን አደረገ? (ቁ.21)
3. የሐጢአት ስሪየት የሚደረግበት ቀን ዓላማው ምን ነበር?

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች  የዚህ በዓል መንፈሳዊ ትርጉም ምንድነው?**

4. ዕብራ፡10፡1-4 አንብብ፡፡ የፍየል መስዋእት ሐጢአታቸውን አስወግዶ ነበር? ከዚህ በዓል የተነሣ ሕዝቡ በየዓመቱ ምን ማስታወስ ነበረባቸው?

5.የሚከተሉትን ክፍሎች አንብብ፡፡ ይህ በዓል ኢየሱስ በመሞቱ የሠራውን ሥራ እንዴት ያሳያል? በፍርድ ቀን ለሐጢአት ስሪየት ከሚሰዋው መስዋእት የኢየሱስ መስዋእትነት እንዴት ይለያል?

ሀ. ዕብራ፡9፡11-14

ለ. ዕብራ፡9፡24-28

ሐ. ዕብራ፡10፡10-18

6. ከክርስቶስ ልደት በኂላ በ70 ዓ.ም ቤተመቅደስ ከፈረሰ በኂላ አይሁድ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት የሚያከብሩትን ይህን በዓል በቀጣይነት አላከበሩም፡፡ ከዛ በኂላ የፍየልና የኮርማ መስዋእት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቀረ፡፡ እግዚአብሔር ይህን ለምን አደረገ? ዕብራ፡10፡10 አንብብ፡፡

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ** **እግዚአብሔር ከእኔ የሚፈልገው ምንድነው?**

1. ዕብራ፡9፡14 እንደገና አንብብ፡፡ የኢየሱስ ደም ለአንተ ምን አደረገ
2. ዕብራ፡10፡19-25 አንብብ፡፡ ይህ ለዘላለም የሐጢአት ስሪየት የተደረገበት ቀን ውጤት ነው፡፡ በዚህ ክፍል መሠረት እኛ ምን አለን? እኛ ማድረግ ያለብን ምንድነው?

## ሰባተኛ፡- የመገናኛው ድንኳን በዓል

**መግቢያ፡-** የመገናኛው ድንኳን በዓል ሌላ መጠሪያው የመሰብሰብ በዓል ነው፡፡ ይህ ያከበሩት በዓል በሰባተኛው ወር ከእርሻቸው እህል ያጨዱበት ቀን መታሰቢያ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምግብ በሌሎች በረከቶች የባረከበት ጊዜ ስለነበረ በሕዝቡ ዘንድ ይህ በዓል እጅግ ታላቅ ደስታን ፈጥሮ ነበር፡፡

**ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)**

1. ዘሌ፡23፡33-34 እና ዘዳ፡16፡13-17 አንብብ፡፡
2. ይህ በዓል የተደረገው መቼ ነበር? በስንት ቀን አለቀ?
3. ወደ በዓሉ መሄድ የነበረበት ማን ነበር? ዘዳ፡16፡14
4. በእነዚህ ቀናት ሕዝቡ ያደረጉትን ግለጽ፡፡
5. በዓሉ እስከሚያልቅ የት መቆየት ነበረባቸው? ለምን? በዚህ በዓል ሕዝቡ ምን እያስታወሱ ማክበር ነበረባቸው? ዘሌ፡23፡42-43
6. እነሱ ለእግዚአብሔር ማቅረብ የነበረባቸው መስዋእት ምን ነበር?
7. ስለ እግዚአብሔር ማስታወስ የነበረባቸው ምን ነበር?

**ትርጉም**፡ የበዓል ትርጉም ምንድነው?

1. እሥራኤላዊያን በምድረ በዳ በድንኳን ውስጥ ለ40 ዓመታት ኖሩ፡፡ ይህ ድንኳን ጊዜአዊና ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀስ ነበረ፡፡ ከዚህ ከድንኳን ኑሮ እሥራኤላዊያን የተማሩት ምንድነው?
2. በመጨረሻው በዓል ቀን ሕዝቡ ሁለት ነገሮችን አደረጉ ፡፡
   *ሀ. ሕዝቡ ችቦ ይዘው ቤተመቅደሱን ዞሩ፡፡ ከዚያም በቤተመቅደሱን ግድግዳ ዙሪያ እሳት ለኮሱ፡፡*
   *ለ.* ካህኑ ከሰሊሆም ውሃ ቀድቶ ወደ ቤተመቅደሱ ያመጣ ነበር፡፡
3. ዘፀ፡17፡1-17 አንብብ፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ሰጠ በዚህ በዓል ምን ማስታወስ ነበረባቸው?
4. ዘኀል፡14፡14 አንብብ፡፡ ሕዝቡን ስለ እሳቱ አምድ ያስታወሰው የትኛው በዓል ነበር?

**<u>የዚህ በዓል ትንቢታዊ ጠቀሜታው ምንድነው?</u>**

5. ዮሐ፡8፡12 አንብብ፡፡ ኢየሱስ ይህንን ሲናገር ችቦው በቤተመቅደሱ ዙሪያ ይበራ ነበር፡፡ ችቦው የእግዚአብሔርን ክብርና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መሆኑንና ሕዝቡን ያሳስባል፡፡ በዚህ ክፍል ኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው ምን ነበር?
6. ኢየሱስ በመጨረሻው ቀን ወደ መገናኛው ድንኳን በዓል በመጣ ጊዜ ሕዝቡን ጠራ፡፡ ዮሐ፡7፡37-38 አንብብ፡፡ ከዚህ ምን ትማራለህ?
7. የዚህ በዓል ትንቢታዊ ጠቀሜታው ወደ ፊት የሚፈጸም መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያሉትን ክፍሎች አንብብና ይህ በዓል ወደ ፊት እንዴት እንደሚፈጸም ተወያይ፡፡
   *ሀ.* ዮሐ፡4፡34-37 አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል የሚሰበሰበው ምንድነው?
   ለ. ዘካ፡14፡4, 9, 16-17 ይህ ክፍል የሚናገረው ክርስቶስ በምድር ላይ ለ1000 ዓመት መንገሡን ነው፡፡ በዚህ በ1000 ዓመት (በሚሊኒየም) ክርስቶስ ኢየሩሳሌምን ይገዛል፡፡ በዚህ ጊዜ የዓለም ሕዝብ በሙሉ ይህንን የመገናኛ ድንኳን በዓል እንዲያከብር ይታዘዛል፡፡ ወደዚህ በዓል የማይመጣ ሁሉ በጌታ አያምንም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ለሕዝባቸው የሚዘንበውን ዝናብ ይከለክላል፡፡
   ሐ. ራዕ፡7፡9-10 አንብብ፡፡ ሕዝቡ የቆሙት የት ነው? ከየትስ መጡ? በእጃቸው የያዙት ምንድው? ማር፡11፡8-10 አንብብ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ለጌታ ቅጠላ ቅጠልና ዘንባባ ያነጠፉበት ሌላኛው ጊዜ የቱ ነበር?

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**፡ ከዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለሕይወቴ የሚያስተምረኝ ምንድነው?

1. የመገናኛ ድንኳን በዓል ከሌሎች በዓላት ልዩ የሚያደርገው ኢየሱስ ሲነግሥ የሚከበር በዓል መሆኑ ነው፡፡ ይህ በዓል የመጨረሻውን የነፍሳት ወደ ጌታ መምጣት ያሳያል፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ያመኑ ሕዝቦች ሁሉ የመንግስተ ሰማያት ደስታ በረከት ይካፈላሉ፡፡

የሚከተለውን አንብብና ተወያይ፡፡

ፋሲካና የቂጣ በዓል----- ክርስቶስ ለሐጢአት በመሞቱ ተፈጽሟል፡፡
ለሐጢአት ይቅርታ የተደረገበት ቀን በዓል------ በክርስቶስ በማመን ተፈጽሟል
የበኩራት በዓል------- በክርስቶስ ትንሣኤ ተፈጽሟል፡፡
የጴንጠቆስጤ በዓል--------በመንፈስ ቅዱስ መምጣት ተፈጽሟል፡፡
የመለከት ድምጽ በዓል----- በክርስቶስ ዳግም ምፃት ተፈጽሟል፡፡

2. የመገናኛ ድንኳን በዓል ክርስቶስ በምድር ላይ በሚነግሥበት ጊዜ መከበሩን ይቀጥላል፡፡ በዚህ ጊዜ ቤተክርስቲያን ይህንን በዓል የሚታከብረው ምን በማድረግ ነው? ይህ በዓል ከብሉይ ኪዳን ዘመን የሚያስታውሰን ምንድነው?

3. በዚህ በመጨረሻው የነፍሳት ወደ ጌታ መሰብሰብ ውስጥ እኛ መግባት የምንችለው እንዴት ነው
4. እሥራኤላዊያን ወደ እግዚአብሔር ፊት ከሚቀርቡባቸው ሦስት በዓላት አንዱ ነው፡፡ ይህ በዓል የእግዚአብሔርን ባህሪያትና ለሕዝቡ ያደረጋቸውን ነገሮች ለታላላቆችና ለታናናሾች ያስተምራል፡፡ በየዓመቱ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መስጠት ነበረባቸው፡፡ በእምነታችን ምክንያት ይህንን በዓል በደስታ በማክበር ልጆቻችንን ማስተማር አለብን፡፡

ሀ. የእግዚአብሔርን መልካምነት ልናከብር የምንችልባቸውን የተለዩ ቀኖች ተወያዩ፡፡
ለ. ልጆቻችንን ለማስተማር ይረዳን ዘንድ ልንፈጥር የምንችለው የቤተሰብ ባህል ምንድነው?